# ከዓባይ ወዲያ ዘመድ

አሥራደው (ከፈረንሳይ)

ዓባይ ! ዓባይ ! ዓባይ ! እያሉ « አባዮች » (እዚህ ጋ ባ ላላ ብላ ትነበብ) የወገኖቻችንን ነብስና ሥጋ አደረቁት፤ በውጪ ካለው ኢትዮጵያዊም በዓባይ ስም ለመቅፈፍ የተሰማራው ሆድ አደር ሠራዊት ባዶ አቁማዳውን እንደሸከፈ ዝንብ ወሮት ተመለሰ፤ ኢትዮጵያ ዛሬም ጀግኖች ለመውለድ ማሕጸኗ አለመድረቁን አዩት፤ እሰይ ያገሬ ልጆች በርቱ እንበርታ፤ ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !!

ዓባይ « በአባዮች » (እዚህ ጋ ባና ዮ ጠበቅ ብለው ይነበቡ) ሳይሆን ሃቀኛ፤ የሕዝብ ፍቅር፤ የአገር ክብርና ለዜጎች መብት መከበር የቆመ ሕዝባዊ መንግሥት በአገራችን ሲቋቋም ፤ ዓባይን በገንዘብ ሳይሆን ባጥንታችን እንገድበዋለን፤ እስከዚያው ድረስ ካባይ ወዲያ ዘመድ ላሳር ነውና ፡ ተውን ።

ዓባይ ከልባችን ደም እየቀዳ፤ ከአካላችን ሙዳ ሙዳ ሥጋ እየቦጨቀ፤ መፍሰሱን እናንተ ሳትነግሩን በፊት እናውቀዋለን « ዛሬ በዓባይ አመካኝቶ ሊበላ ተነጉቶ ? »
እስቲ በመጀመሪያ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የዘረፋችሁትን 8.5 ቢሊዮን ዶላር፤ የመንግሥት የነበሩ ተቋማትን ወደ ግል ማዘዋወር፤ (privatisation) በሚል ሰበብ የተዘረፈውን፤ ድሃ ገበሬ እየተፈናቀለ ለድንበር ዘለል ከበርቴ መሬት የተቸበቸበበት.... ወዘተ. የት እንደገባ ? ማን እንደዋጠው ? ይነገረን ።

ካባይ ወዲያ እናቴ ፡ ካባይ ወድያ አባት ፤
ካባይ ወዲያ ወንድም ፡ ካባይ ወዲያ እህት፤
ካባይ ወዲያ አጎቴ ፡ ካባይ ወዲያ አክስት ፤
ካባይ ወዲያ አማቼ ፡ ካባይ ወዲያ አማት፤
ካባይ ወዲያ ምራት ፡ ካባይ ወዲያ አያት፤
ካባይ ወዲያ ጓዴ ፡ አጋር የልጅነት፤
አገኛለሁ ብሎ ጧት ማታ መልፋት፤
ዋ ! ብሎ መቅረት ነው ከንቱ መዋተት ።

ካባይ ወዲያ ታማኝ ፡ የሰው ልጅ አፍቃሪ፤
ካባይ ወዲያ እጨኛ ፡ ቃል ኪዳን አክባሪ፤
ካባይ ወዲያ ደራሽ ፡ የቅርብ ጎረቤቴ፤
ካባይ ወዲያ ባሌ ፡ ካባይ ወዲያ ሚስቴ፤
ካባይ ወዲያ ልጄ ብሎ መጣራት፤
እንዳው በከንቱ ነው ቀን ቢጎልበት ።
ካባይ ወዲያ ዘመድ ካባይ ወዲያ አጋር፤
አገኛለሁ ብሎ አለመናገር ነው አለ መጠርጠር ።

አንድ ቀን

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!
እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይባርክ !!

EthioLion.Com